**ገደብ የሌለው የልደቱ ውሸትና አላማው።**

አቶ እስክንድር ነጋ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋና የልደቱ ውዝግብ በሚል ርዕስ በኢትዮሚድያ ላይ ያወጣውን ጽሑፍ ካነበብኩ በኋላ እኔም አንድ ሲከነክነኝ የነበረን ነገር ህዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ ተገደድኩ። ስለልደቱ ብዙ የማወቀው ነገር ቢኖርም በወደቀው ዛፍ ላይ ከተነሱበት ምሳሮች መሃል ራሴን ላለመመደብ ስል ትቼዋለሁ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ወደፊት የምመለስበት ይሆናል። ልደቱ "አንድ ኢትዮጵያ" በሚባለው የወያኔ የዲሲ ራዲዮ ጣቢያ ላይ የተናገራቸው ብዙ ውሸቶች ቢኖሩም በዚህኛው ጽሑፌ የማተኩረው በአንዱ ጉዳይ ይሆናል። ለዚህም ተጨባጭ ማስረጃ አቅርቤ ልደቱ ቀጣፊ መሆኑን አንባቢዎቼ እንዲረዱልኝ አደርጋለሁ። በመጨረሻም የቅጥፈቱ አላማ ምን እንደሆነ ገልጬ ጽሑፌን አበቃለሁ።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የምርጫ 97 ሰማእታትን ለመዘክር ዲሲ ላይ ተደረጎ በነበረው ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ልደቱን በሚመለከት የሚከተለውን (ቃል በቃል ባልጠቅሰውም) ብለው ነበር።

"ልደቱ የ97ቱ ምርጫ ከተጭበረበረ በኋላ ቅንጅት ምን ያድርግ ለሚለው ጥያቄ የሰጠው መልስ ህዝብ ለተቃውሞ እንዲወጣ ጥሪ እናደርጋለን፣ ህዝቡም የምናደርገውን ጥሪ ሰምቶ ይወጣል፣ ኢህአዴግም ህዝቡን ይገላል፣ ብዙዎችንም ያስራል፣ እኛም ኢህአዴግ የሚወስዳቸውን የግድያ እና የእስራት እርምጃዎች ሰበብ አድርገን ያለው አማራጭ ፓርላማ ግብቶ በሰላም መታገል እንደሆነ ገልጸን ፓርላማ እንገባለን ብሎ ነበር።"

ዶ/ር ብርሃኑ በዲሲው ስብሰባ ላይ ልደቱን ያለምክንያት ዝም ብለው አላነሱትም። ራሱ ልደቱ ሰማእታቱን ለማስታዎስ የሚደረግን ስብሰባ አራክሶ መናገሩን መንስኤ አድርገው እንዳነሱ በንግግራቸው አሳውቀውናል። ልደቱ "በአንድ ኢትዮጵያ" የዲሲው የወያኔ ራዲዮ በሰጠው ቃለ ምልልስ በሰማእታቱ ጉዳይ ላይ የተናገረው ነገር እንደነበር አልካደም። በዚህ ራዲዮ ጣቢያ ላይ ልደቱ ከዛም በላይ አልፎ ሌላም ሌላም ነገር ተናግሯል። ቃል በቃልም ራሱን ሲከላከል እንዲህ ብሎ ነበር፤

"ሰው ይሙትና ፓርላማ እንግባ የሚል ሃሳብ ፈጽሞ አላቀረብኩም። እንዲህ አይነቱን ጉድ ተናግሬ ቢሆን ኖሮ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ለማጋለጥ 5 አመት ምን አስጠበቃቸው? ለምን ቀደም ብለው አላቀረቡትም? ይህ በራሱ እኔን ለማጥቃት ፈጠረው የሚያወሩት ነጭ ውሸት ለመሆኑ አንድ ማስረጃ ነው።"

እንግዲህ ልደቱ ይህንን ሲል ሁለት ነገር ነው የታየኝ። ይህን ክስ ለመጀመሪያ ግዜ ነው የሰማሁት በማለት እየዋሸን ነው። ወይም የሬድዮኑ አድማጭ ይህ ክስ የተሰነዘረበትን የቀደሞ መረጃ ማግኘት አይችልም ብሎ አድማጬን ለማጭበርበር የሰነዘረው ቅጥፈት ነው።

ልደቱ "ሰው አስገድለን ፓርላማ እንግባ የሚል ሃሳብ አቅርቦ እንደነበር ዶ/ር ብርሃኑ ለመጀመሪያ ግዜ አልነበረም በዲሲው ስብሰባ የተናገሩት። ይህን ለመናገር ልደቱ በወያኔ ራዲዮ እንዳቀረበው አምስት አመት አልቆዩም። በ98 ዓ.ም የቅንጅት መሪዎች እስር ቤት በተወረወሩ ጥቂት ወራት ውስጥ እዛው እስር ቤት ሆነው በጻፉት የነጻነት ጎህ ሲቀድ በሚለው ግሩም መጽሃፍ ላይ በሚገባና በዝርዝር አትተውበታል። የነጻነት ጎህ ሲቀድ የሚለው የዶ/ር ብርሃኑ መጽሃፍ ከገጽ 371 እስከ 378 ያተኮረው በዚሁ ነውረኛ የልደቱ አስተሳሰብ ላይ ነው።

እኔም የልደቱን የውሸት ክርፋት ለሰሙ ሁሉ የሰውየውን የቅጥፈትና የክህደት ጥልቀት ማየት ይችሉ ዘንድ ዶ/ር ብርሃኑ በመጽሃፋቸው በገጽ 374 ላይ ያሰፈሩትን በተለይ በዲሲው ስብሰባ ላይ ካቀረቡት ምንም ልዩነት ስለሌለው የመጽሃፉን ገጽ እንዳለ ፎቶ ኮፒ አድርጌ ለአስረጂነት እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

እንግድህ እውነቱ ይህ ነው። አይታወቅብኝም በሚል ልደቱ ቀጠፈ። የልደቱ ቅጥፈትና በወያኔ ሚድያዎች በመቅረብ እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የመሳሰሉትን ግለሰቦች ውሸታሞች ናቸው የሚል ክስ መደርደር ዓላማው ምንድን ነው? የልደቱ አዲሱ ተልዕኮስ ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያደርገናል።

በእኔ እምነት መልሱ ቀላል ነው። የወያኔን ውሸታምነትና ይሉኝታ ቢስነት በማጋለጥ ከታወቁት መሃል አንዱ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ናቸው። በወያኔ ዘመን አንድ ትውልድ እውነት ሳይሰማ ውሸት እየተነገረው እያለፈ ነው የሚለው አባባላቸው የህዝብን ስሜት መኮርኮሩ ይታወቃል። የወያኔን ባለስልጣናትም እጅግ የሚያቃጥል ጉዳይ ነው:: ዶ/ር ብርሃኑ በምርጫው ወቅትና ከምርጫው በኋላ በማስረጃ እያሰደገፉ እንዴት መለስ ዜናዊና የውጭ ጉዳይ ሚንስትር የነበረው ስዩም መስፍን እንዲሁም ሌሎች የአገዛዙ ባልስልጥናት አይናቸውን በጨው ታጥበው የሚዋሹ ቀጣፊዎች መሆናቸውን ለህዝብ አስረድተዋል። በሃገር ደህንነትና ጥቅም ላይ እንደሚዋሹ፣ በኢኮኖሚ እድገት ቁጥር እንደሚዋሹ፣ በገደሉአቸውና ባሰሩአቸው ሰዎች ብዛት ላይ እንደሚዋሹ፣ ወያኔዎች ቃል ማክበር የሚባል ነገር እንደማይገዳቸው ፣ ዛሬ የተናገሩትን ነገ ለመካድ ይሉኝታ የሚባል ነገር ያልዘራባቸው ለመሆናቸው የዶ/ር ብርሃኑን ያህል አምርሮ የከሰሳቸው ሰው የለም።

የልደቱ አዲሱ ተልእኮ የወያኔን ውሸታምነት የሚያጋልጡትንና ህዝብ ያዳምጣቸዋል የተባሉትን ግለሰቦች እራሳቸው ሊታመኑ አይገባም የሚል የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ በሃገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ እንዳይደመጡ ለማድረግ ነው። ከላይ እንዳሳየሁት ግን ይህን ስራ ለመስራት በቅጥረኛነት የሚመጡ ሰዎች በሚገባ የቤት ስራቸውን ሰረተው ስለማይመጡ እራሳቸውን አዋርደው ጌቶቻቸውን አክስረው ይመለሳሉ። ልደቱም እንደማንኛውም የወያኔ ጀሌ ያተረፈው የበለጠ ውርደትን ነው። "አድርጌው ቢሆን ኖሮ ይህን የኔን ጉድ ለማውጣት ለምን አምስት አመት ዶ/ር ብርሃኑ መጠበቅ አስፈለገው" በማለት ጉዳዩን በፈጠራ ማስረጃነት ለማቅረብ ሙከራ ሲያደርግ ያልተረዳው ለራሱ ቀጣፊነት ማስረጃ እያቀረበ እንደነበር ነው። "ሰው አስግድለን ፓርላማ እንግባ" የሚለውን የልደቱን ፋሽታዊ አመለካከት የሰማነው ትናንት አልነበረም። አንዳንዶቻችን ልደቱ ይህን በተናገረበት ስብሰባ ላይ ነበርንና ልደቱ ይህን ለማለቱ የዶ/ር ብርሃኑ መጽሃፍ መጥቀስ አያስፈልገንም።

ንጋትና ውሸት እያደር ይጠራል ይባል የለ።

ከቀድሞ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት አንዱ።